ክፋት ለምን ተፈቀደ? እንዴት ተጀመረ? መጨረሻውስ?

ከዘላለም እስከ ዘላለም እግዚአብሔር ፍቅር ነው

ክፍል 1 - ክፋት ለምን ተፈቀደ?

ክፋት ለምን?

- ስቃይ ያስከተለው ቀውስ
  - The Crisis of Suffering
- የፍጥረተ ዓለም ግጭት መድረክ
  - The Arena of the Cosmic Conflict
- ፍቅር፡ ነጻ ፈቃድ እና የእግዚአብሔር ፈቃድ

ኤፊቆሮስ (Epicurus)

- Is God willing to prevent evil, but not able? Then he is not omnipotent. Is he able, but not willing? Then he is malevolent. Is he both able and willing? Then whence cometh evil? Is he neither able nor willing? Then why call him God?
- **እግዚአብሔር ክፉን/ክፋትን ማስቆም ይፈልጋል ግን አይችልም (አቅም የለውም)? ከሆነ ሁሉን ቻይ አይደለም:: ወይስ ክፉን ማስቆም ይችላል ግን አይፈልግም? ከሆነ ክፉ እንዲሆን የሚፈልግ ተንኮለኛ ነው ማለት ነው:: ወይስ ክፉን ማስቆም የሚፈልግም የሚችልም ነው? ከሆነ ታዲያ ክፋት ከየት መጣ? ወይስ ክፋትን የማስቆም አቅሙም ፍላጎቱም የለውም፤ ከሆነ ታዲያ ለምን አምላክ ተብሎ ይመለካል?**
- **መዝሙር** 10፥ **አቤቱ÷ ለምን ርቀህ ቆምህ? በመከራም ጊዜ ለምን ትሰወራለህ?**

ክፉት ያመጣው ዓለምአቀፋዊ እውነታዎች

- በየቀኑ 24,657 ሰዎች ከረሃብ ጋር በተያያዙ ምክንያቶች ይሞታሉ
  - በየ 10 ሰከንዱ አንድ ሕፃን ይሞታል
- በአሜሪካ በየዓመቱ ዕድሜያቸው 12+ የሆኑና ወሲባዊ ጥቃት የሚደርስባቸው
  - 463,634 ሰዎች
  - በየ 68 ሰከንዱ አንድ ሰው (RAINN)
- በየዓመቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ 1.25 ሚሊዮን ሰዎች በግድያ፣ ራሳቸውን በማጥፋት ወይም በግጭት/ጦርነት ይሞታሉ (WHO)
  - በየቀኑ ከ3,400 በላይ ሰዎች
- በየዓመቱ 51,100 ሴቶች እና ልጃገረዶች በሚወዷቸው ሰዎች ወይም ቤተሰብ ይገደላሉ
  - በየቀኑ 140
  - አደገኛው ቦታ የመኖሪያ ቤት ሆኗል

“እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ይቆጣጠራል” ከሚለው አሰተሳሰብ የሚነሳ ችግር

- “ውሻዬ ለምን ሞተ”?
- እግዚአብሔር ውሻዬን የገደለው ቀጥሎ አያቴን ሊገድል እየተዘጋጀ ስለሆነ ነው
- ይህ ዓይነቱ ቀለል ያለና የተሳሳተ ትምህርት የእግዚአብሔርን ባሕርይ የተዛባ አመለካከት እንዲኖረን ያደርጋል።



በመለኮታዊ ፍትሕ እና በሰው ልጅ ሰቃይ መካከል ያለው ትግል

- ኢዮብ መልካም ሲጠብቅ ክፋ መምጣቱን ይናገራል (ኢዮብ 30፡26)
  - “በጎነትን በተጠባበቅሁ ጊዜ ክፋ ነገር መጣችብኝ”
- ኤርምያስ የኃጢአተኞች መንገድ ለምን እንደሚቀና ይጠይቃል (ኤርምያስ 12፡1)
  - “የኃጢአተኞች መንገድ ስለምን ይቃናል?”
- ባለ መዝሙሩም ይጠይቃል (መዝሙር 10፡1)
  - “አቤቱ÷ ለምን ርቀህ ቆምህ? በመከራም ጊዜ ለምን ትሰወራለህ?”
- “እግዚአብሔርን በቃላችሁ አታክታችኋል። እናንተም፦ ያታከትነው በምንድር ነው? ብላችኋል። ክፉን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ መልካም ነው÷ እርሱም በእነርሱ ደስ ይለዋል፤ ወይስ፦ የፍርድ አምላክ ወዴት አለ? በማለታችሁ ነው” ሚልክያስ 2፡17።

ለሰው ልጅ ጥያቄ እግዚአብሔር የሚሰጠው መልሰ

- እግዚአብሔር በጥያቄ ይመልሳል
- “እግዚአብሔር ከዐውሎ ነፋስ ሆኖ ለኢዮብ ይመልሳል፥ ያለ እውቀት በሚነገር ቃል ምክርን የሚያጨልም ይህ ማነው?” (ኢዮብ 38፥1-2)።
  - “ይህ÷ ያለ ዕውቀት በሚነገሩ ቃላት ምክሬን የሚያቃልል እርሱ ማነው?”
  - “ጥቂት ብቻ የምታውቅ ሆነህ ሳለ ለምን ብዙ ታወራለህ?" (CEV)
- “የምድር መሠረት ጣልኩ ጊዜ የት ነበርህ?” (ኢዮብ 38፥4)።
- ይህም የእግዚአብሔርን ጥበብ ማለቂያ የሌለው መሆን እና የሰው ልጅ አእምሮ ውስንነት ያሳያል።
  - ስለዚህ ይህንን የፍትሕ ጥያቄ ስንጠይቅ ትሕትና ያስፈልጋል

የመለኮታዊ ጥበብ ምሥጢር

- **መለኮታዊ መገለጥ** (Divine inspiration) **እጅግ የመጠቁ ሊቃውንት እንኳ ሊመልሷቸው የማይችሏቸውን በርካታ ጥያቄዎችን ያነሳል። እነዚህ ጥያቄዎች የቀረቡት እኛ መልስ እንሰጣቸዋለን በሚል እሳቤ ሳይሆን፣ ልባችን ወደ እግዚአብሔር ጥልቅ ምሥጢራት እንዲያዘነብልና የሰው ልጅ የጥበቡን ውሱንነት እንዲረዳ ለማድረግ ነው፤ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ተራ በሚመስሉ ነገሮች ውስጥ እንኳ ውሱን በሆነው የሰው አእምሮ ሊደረስባቸው የማይችሉ ምሥጢራት መኖራቸውን፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር የፍትሕ አሠራርና ዓላማዎች በምርምር ብቻ የማይደረስባቸው፣ ጥበቡም እጅግ ጥልቅና ረቂቅ መሆኑን ለማሳየት ነው። አምላክ ራሱን ለሰው ልጅ የሚገልጠው፣ ራሱን ጥቅጥቅ ባለ ታላቅ የምሥጢር ደመና በመጋረድ ነው።**
- Divine inspiration asks many questions which **the most profound scholar cannot answer**. These questions were not asked, supposing that we could answer them, **but to call our attention to the deep mysteries of God**, and to make men know that their wisdom is limited; that **in the common things of daily life there are mysteries past the comprehension of finite minds**; that the judgment and purposes of God are past finding out, **His wisdom unsearchable**. **If He reveals Himself to man, it is by shrouding Himself in the thick cloud of mystery**.—Ellen G. White Comments, in The Seventh-day Adventist Bible Commentary, vol. 3, p. 1141.
- **ካልተመለሱ ጥያቄዎች ጋር የመኖር ልምምድ**
  - **በእምነትና በተስፋ ለመጓዝ አስፈላጊ አካል ነው።**

የክፋትና የሥቃይ ምሥጢር/እንቆቅልሽ

- **“የዓመፅ ምሥጢር” 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡7**
- **“ለብዙ ሰዎች የኃጢአት መነሻና የመከሰቱ ምክንያት እጅግ አደናጋሪና አሻሚ የሆነ እንቆቅልሽ ነው። የክፋትን መስፋፋት እንዲሁም እየስከተለ ያለውን አስከፊ መከራና ውድመት በሚመለከቱበት ጊዜ፤ በጥበቡ፣ በኃይሉና በፍቅረ ወሰንየለሽ በሆነው ኃያል አምላክ መለኮታዊ ሉዓላዊነት ሥር ይህ ሁሉ እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ይጠይቃሉ። ይህ ለእነርሱ ምንም ዓይነት ማብራሪያ ሊያገኙለት ያልቻሉበት ታላቅ ምሥጢር ነው”።**
- "To many minds the origin of sin and the reason for its existence **are a source of great perplexity**. They see the work of evil… and they question how all this can exist under the sovereignty of One who is infinite in wisdom, in power, and in love. Here is a mystery of which they find no explanation." — Ellen G. White, *The Great Controversy*, p. 492.

Theodicies on the Problem of Evil

- Theodicy
  - *theos* [God/አምላክ] + *dike* [justice/ፍትሕ])
  - መከራ ባለበት ዓለም ውስጥ የእግዚአብሔርን ቸርነት፣ መልካምነት፣ ፍቅር እና ፍትሕ ለማስረዳት የሚደረግ የነገረ-መለኮት ዘርፍ ነው።
- ይህ ሁሉ መከራ፣ ሰቆቃ፣ ችግር፣ ስቃይ በሞላበት ዓለም ውስጥ እንዴት ሁሉን የሚገዛው፣ ኃያልና ሉዓላዊ አምላክ እግዚአብሔር ጻድቅ፣ ቅን ፈራጅ እና አፍቃሪ ሊባል ይችላል

Theodicies on the Problem of Evil

- **Greater-Good Theodicies**
  - Evil serves a higher purpose
  - **Certain evils are necessary for greater goods that could not occur otherwise**
- **Privation Theory (Augustinian Theodicy)**
  - Evil is not a thing, but absence of good
  - Evil results from turning away from God, not created by Him

Theodicies on the Problem of Evil

- **Skeptical Theism**
  - Human knowledge is limited
  - We cannot judge God's reasons; apparent gratuitous evils may serve unknown purposes
- **Free Will Defense**
  - Humans have genuine freedom
  - Evil arises from human **misuse of free will**; **God allows this to preserve freedom**
- Eschatological Theodicy; Mysterious / Ironic Theodicy; …

የኮሰሚክ ግጭትን Cosmic Conflict ለመረዳት

- የኮስሚክ (የፍጥረተ ዓለም) ግጭት ባሕርይ
  - Nature of the Cosmic Conflict
- የእግዚአብሔር ሕዝብ ተሳትፎ
  - Involvement of God's People
- የኮስሚክ ግጭት መደምደሚያ
  - Resolution of the Cosmic Conflict

የኮሰሚክ ግጭት ባሕርይ

- ግጭቱ ሁለት የአቻ ኃይላት ትግል አይደለም።
  - የyin-yang ዓይነት
- ግጭቱ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ባሕርይ እና ጽድቅ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሞራላዊ ጥያቄ ነው።
- ሉሲፈር በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው
  - በእግዚአብሔር ባሕርይና የጽድቅ አሠራር ላይ ጥያቄ በማንሳት ዓመፅ አስነስቶአል
  - ይህ ማለት ግን ሁለቱ ተፋለሚ ኃይላት እኩያ አይደሉም
  - አንዱ ፈጣሪ ሌላው ተፈጣሪ ነው



“ፓንቶክራቶር” (*Pantokrator*)

- ሁሉን ቻይ/ገዢ) ("All-Powerful")
- ራእይ ላይ እግዚአብሔርን “ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ” (*Pantokrator)* ብሎ ይጠራዋል።
  - ራእይ 11:17፣ 1:8፣ 16:14፣ 19:15፣ 21:22
- እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ መሆኑ ማለት ሰዎችን በግድ (by coercion) ይቆጣጠራል ማለት አይደለም።
- ፓንቶክራቶር ማለት ፍጡራኑን በነጻ ፈቃዳቸው እንዲኖሩ እየፈቀደ፣ ዓለማውን በፍቅር የሚፈጸም ሱፕሪም (Supreme) ገዢ ማለት ነው።

የእግዚአብሔር ፍጹም ነጻ እና እጅግ ሰፊ ፍቅር

- እግዚአብሔር ዓለምን የፈጠረው ከፍቅር በመነጨ ፍላጎት እንጂ ለባርነት ወይም ለሌላ ዓላማ አይደለም።
- ፍጥረት የእግዚአብሔር እጅግ ለጋስ የሆነው ፍቅሩ መገለጫ ነው።
  - ከውድቀትም ሆነ ከኃጢአት ጋር የተያያዘ አይደለም
  - እግዚአብሔር እንዲፈጥር ያደረገው ወይም ያስገደደው የለም
- እግዚአብሔር ለዘላለም ፈጣሪ ሆኖ ለመኖር ፍጥረት የግድ አያስፈልገውም
- ከፍጥረት በፊት ሥላሴ በአንድነት እና ፍጹም ፍቅር ይኖሩ ነበር
  - ዮሐንስ 17፥24

ፍቅር፣ ነጻ ፈቃድ እና የእግዚአብሔር ፈቃድ

- ክፋት የሚመጣው ፍጡር የተሰጠውን ነጻ ፈቃድ (free will) አላግባብ በመጠቀሙ ነው እንጂ ከእግዚአብሔር ፈቅዶት የመጣ አይደለም።
  - ሮቦቶች (Automatons) ፍቅር ሊኖራቸው አይችልም
  - እውነተኛ ግንኙነት ነጻ ፈቃድን (free will) ይጠይቃል
- ከእግዚአብሔር ጋር የሚመሠረት ግንኙነት፣ ፍጹምና እውነተኛ ደስታ በፈቃደኝነትና በነጻ ፈቃድ ውሳኔ ላይ ብቻ ነው የሚመሠረተው
- እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ፣ ለፍቅር አስፈላጊ የሆነውን ወሰኝ ግብዓት – ነጻ ፈቃድ አያጠፋም/አይከለክልም

ሮቦት ውሻ (Aibo) እና የአሰገዳጅ ታዛዥነት አደጋ

- Aibo: የሶኒ ሮቦት ውሻ (በ1999 ለመዝናኛ የተሠራ)።
- እግዚአብሔር ሰውን ሕጉን እንዳይተላለፍ ለእርሱ ፍጹም ታዛዥ እንዲሆን አድርጎ መፍጠርና ይችል ነበር
- “የሰው ልጅ የምርጫ ነጻነት ባይኖረው ኖሮ፣ ታዛዥነቱ በገዛ ፈቃዱ ሳይሆን በግዴታ የሚሆን ነበር . . . ይህ ደግሞ እንደ አስተዋይና ባለአእምሮ ፍጡር ለሰው ልጅ ክብር የማይመጥን ከመሆኑም በላይ፣ ሰይጣን “የእግዚአብሔር አገዛዝ አስገዳጅና አምባገነናዊ ነው” በማለት ላቀረበው ክስ ማረጋገጫ ይሆን ነበር።” — *Conflict and Courage*, p. 13





ፍቅር በግድ ሊመጣ አይችልም

- ነጻነት የሌለበት የኒቨርስ ፍቅር አልባ የኒቨርስ ነው የሚሆነው፤ እንደዚህ ያለ ዓለም ውስጥ ማንም መኖር አይሻም
- “ምድር እግዚአብሔርን በተሳሳተ መንገድ በመረዳት በጨለማ ተውጣ ነበር። ያ ጥቅጥቅ ያለ ጥላ እንዲገፈፍና ዓለም ወደ እግዚአብሔር እንድትመለስ፣ የሰይጣን የማታለል ኃይል መሰበር ነበረበት። ይህ ደግሞ በኃይል ሊከናወን የሚችል አልነበረም። ግዳጅን ወይም ኃይልን መጠቀም ከእግዚአብሔር መለኮታዊ አገዛዝ መርሆዎች ጋር ፍጹም የሚቃረን ነው፤ እርሱ የሚሻው በፍቅር ላይ የተመሠረተ አገልግሎትን ብቻ ነው፤ ፍቅር ደግሞ በግዳጅ ወይም በትእዛዝ ሊገኝ አይችልም፤ በኃይል ወይም በሥልጣንም ፍቅርን ማግኘት አይችልም። ፍቅር ሊኖር የሚችለው በፍቅር ብቻ ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እርሱን መውደድ ነው፤ በመሆኑም የእርሱ ባሕርይ ከሰይጣን ማንነት ጋር ተነጻጽሮ በግልጽ መታየት ነበረበት። ይህንን ታላቅ ሥራ በመላው ፍጥረተ ዓለም ውስጥ ሊያከናውነው የሚችለው አንድ አካል ብቻ ነበር። የእግዚአብሔርን ፍቅር ከፍታና ጥልቀት በትክክል የሚያውቀው እርሱ ብቻ ስለነበር፣ ያንን ፍቅር ሊገልጠው የሚችለው እርሱ ብቻ ነው። ስለዚህም በዓለም ድቅድቅ ጨለማ ሌሊት ላይ የጽድቅ ፀሐይ “በክንፎቹ ፈውስን ይዞ” መውጣት ነበረበት” ሚልኪያስ 4፡2። — The Desire of Ages, 22